# በኢትዮጵያ የንግድ ሕግና በኢንሹራንስ ፖሊሲ መካከል ያለ አለመጣጣም ፤ በአካል አደጋና በሕይወት ፖሊሲዎች ላይ የተደረገ ልዩ ትኩረት

በበላይነህ ስዩም *

## መ ግ ቢ ያ

ኢንሹራንስ የተለያዩ ስልተ—ምርቶች ውጤት ሲሆን ዓላማውም የአደጋ ሥጋትን ገንዘብ እየተከፈለው እስከተወሰነ ደረጃ ድረስ ሥጋቱን ከግለ—ሰቦች ወደ ራሱ ለመቀበል ፈቃደኛ ወደሚሆን ኢንሹራንስ ሰጪ ማስተላለፍ ነው ። የኢንሹራንስ ውል በአንድ ነገር መሆን ወይም አለመሆን ሁኔታ ላይ የሚመሠረት ሲሆን ኢንሹራንስ ሰጪው በኢንሹራንስ ተቀባዩ ላይ አንድ የተወሰነ ድንገተኛ ጥፋት ፤ ጉዳት ወይም ኃላፊነት ሲደርስበት ያንን ለመካስ ይስማማል ።

ኢትዮጵያ ከውጪው ዓለም ጋር ግንኙነቷን ስታጠናክር ብዙ የውጪ የኢንሹራንስ ኩባንያዎች በአገሪቱ ውስጥ ወኪሎቻቸውን በመመደብ እ.ኤ.አ. 1920 ዓ.ም. አካባቢ የአገር ውስጥ የኢንሹራንስ ንግዳቸውን ጀመሩ ። እነዚህም ወኪሎች የውጪ ዜጐች ሲሆኑ ከነዚህም መካከል ጥቂቶቹ ወደኋላ የዋናዎቹ ኩባንያዎች ቅርንጫፍ የሆኑ ጽ/ቤቶችን ከፍተዋል ። ቢሆንም እነዚህን የኢንሹራንስ ኩባንያዎች የሚመለከቱ ሕጐች የወጡት እ.ኤ.አ. በ1960 ዓ.ም. ነው ። የኢንሹራንስ ሥራ በአገሪቱ ከተጀመረበት ጊዜ ጀምሮ በሥራ ላይ ከዋሉት ፖሊሲዎች ብዙዎቹ በእንግሊዝ አገር ከሚሠራባቸው ፖሊሲዎች የተገለበጡ በመሆናቸው የእንግሊዝ ሕገ—ፍልስፍና ኢንሹራንስን በሚመለከቱ ሕጐች ላይ ተጽዕኖ አድርጓል ለማለት ይቻላል ።

የማንኛውም ዘመናዊ የኢንሹራንስ ዓላማ በሰው ሕይወትና በንብረት ላይ አደጋ ሲደርስ የዚህን አደጋ ጠንቅ ማካካስ ነው ። በአጠቃላይ ሲታይ ያልታሰበ ኪሣራን የማከፋፈያና የማቻቻያ ዘዴ ነው ። ኢንሹራንስ የሚገቡ ሰዎች ይደርስብናል ብለው የሚገምቱትን የአደጋ ጠንቅ ከራሳቸው ወደሌሎች ትከሻ ያስተላልፋሉ ። ኢንሹራንስ ሰጪዎቹም ክፍያ ስለሚደረግላቸው ኃላፊነቱን በፈቃደኝነት የሚቀበሉ ሲሆን በሕይወት ኢንሹራንስ ጊዜ ለጥገኞቻቸው መጠቀሚያ የሚሆን ያዘጋጁላቸዋል ወይም እዳ መክፈል ለሚገባቸው ባለገንዘቦች ገንዘባቸውን የሚያገኙበትን መንገድ ይፈጥሩላቸዋል[1] ።

በዘመናዊ የኢንሹራንስ አሠራር መሠረት ኃላፊነት የሚወሰድለት አደጋ ተለይቶ የታወቀና ሁለቱ ወገኖች የተስማሙበት ሲሆን ኢንሹራንስ ሰጪውም አደጋው በደረሰ ጊዜ ለሚከፍለው ካሣ ኃላፊነት በመውሰዱ አረቦን (ፕሪሚየም) ተብሎ የሚጠራ ክፍያ ይደረግለታል ። በፖሊሲው ውስጥ አንዳንድ ሁኔታዎች ፤ መድኖችና ልዩነቶች አሉበት ። እነዚህም የኢንሹራንስ ሰጪውንና የኢንሹራንስ ገቢውን ግዴታና ኃላፊነት የሚዘረዝሩ ናቸው ። ከዚህም በስተቀር የኢንሹራንስ ሥራን የሚመለከቱና የኢንሹራንስ ገቢውን መብት በኢንሹራንስ ሰጪው እንዳይደፈሩበትና የኢንሹራንስ ሰጪውም ጥቅም አለአግባብ በኢንሹራንስ ገቢው እንዳይነኩ የሚከላከሉለት ድንጋጌዎች በንግድ ሕግ ውስጥ ተጽፈዋል ።

በንግድ ሕጉ ውስጥ ኢንሹራንስን የሚመለከቱት ድንጋጌዎች የተረቀቁት የኮንቲኔንታል የሕግ ሥርዓትን በሚከተሉ የሕግ ምሁር በመሆኑ የፈረንሳይና የጣልያን የኢንሹራንስ ሕግ በኢትዮጵያ የኢንሹራንስ ሕግ ላይ ተጽዕኖ አድር ገዋል ። ሆኖም የኢንሹራንስ ጽንሰ ሀሳብና ልምዱም በመሠረቱ የመነጨው በእንግሊዝ አገር በመሆኑ የኮንቲኔንታል የሕግ ባለሙያዎች አመለካከት ላይም እንኳን ቢሆን በዚህ በኩል የእንግሊዝ ሕግ—ፍልስፍና ትልቅ ተጽዕኖ ማድረጉ አልቀረም[2] ። ሌላው እውነታ ደግሞ የኢትዮጵያ የኢንሹራንስ ንግድ አብዛኛ ውን በሎይድስ (ግዙፉ የእንግሊዝ የኢንሹራንስ ንግድ ድርጅት) ቁጥጥር ሥር ስለነበር ከትንሽ ለውጥ በስተቀር ፖሊሲዎቹ በእንግሊዝ አገር ከሚሠራባቸው የኢንሹራንስ ፖሊሲዎች ጋር ተመሳሳይነት ያላቸው መሆኑ ነው ። በነዚህ ፖሊ ሲዎች ላይ አልፎ አልፎ የተደረጉት ጥቂት ለውጦችም ቢሆኑ በፖሊሲዎቹና በኢንሹራንስ ሕግ መካከል ብዙም መስማማት አላስገኙም ። ይህ አለመጣጣም በተለይም የኢንሹራንስ ኩባንያዎች በመንግሥት ቁጥጥር ሥር ከዋሉ ወዲህ ከፊተኛውም ይበልጥ ጕልቶ ይታያል[3] ። ይህ ጽሑፍ ከሕጉ ጋር በማይጣጣሙ ስድስት ዋና ዋና ጉዳዮች ላይ ትኩረት የሚያደርግ ነው ። ይኸውም የአረቦን ክፍያን ፤ የይርጋ ጊዜን ፤ አስፈላጊ የሆነ ጉዳይ መደበቅን ፤ የአደጋ ሥጋት መጨ መርን ፤ የሕይወት ኢንሹራንስንና ተደራራቢ ኢንሹራንስን የተለየ ትኩረት በመስጠት በሠፊው ይመለከታል ።

## 1. ስለ አረቦን ክፍያ

የአረቦን ክፍያን በሚመለከት ረገድ ለኢንሹራንስ ገቢው ጥቅም ሲባል ውሉ በድንገት እንዳይቋረጥበት የሚከላከልለት ድንጋጌ በንግድ ሕጉ ውስጥ ሠፍሯል ። በዚህም መሠረት ኢንሹራንስ ሰጪው ውሉን ሳያቋርጥ ክፍያው እስ ኪደረግ መጠበቅ ያለበት ጊዜ በሕጉ ተወስኗል ። ከዚህ ከተወሰነው ጊዜ በሚቀ ጥለው አንድ ወር ውስጥ የኢንሹራንሱ ውል እንዲታገድ ብቻ ይደረጋል ። ይህ አሠራር የመንግሥት ፖሊሲ በመሆኑ በሁለቱ ወገኖች ስምምነትም እንኳን ቢሆን ሊሻሻል አይችልም[4] ። በዚህ ፖሊሲ መሠረት የንግድ ሕግ ቁ. 666(2) እንዲህ ይላል ፤ «ተቃራኒ ስምምነት ቢኖርም እንኳ ተጠቃሚው ለኢንሹራንስ መግቢያ የሚከፈለውን ገንዘብ በተወሰነው ጊዜ ባለመክፈሉ ብቻ ውሉን ለማ ፍረስ አይቻልም ። ኢንሹራንስ ሰጪው ገንዘቡ እንዲከፈለው መጠየቅ አለበት ።»

ቢሆንም ቁ. 666 ይህ ድንጋጌ በእንዴት ያሉ ሁኔታዎች ሥራ ላይ እንደሚ ውል ግልጽ አድርጐ አይናገርም ። ቁ. 666 ተፈጻሚነት የሚኖረው በየጊዜው ለሚከፈል አረቦን ሆኖ የውሉ ጊዜ ከማለቁ በፊት ክፍያው ሲቋረጥ ነው ወይንስ ውሉ ከተቋረጠ በኋላ እድሳት ሲጠይቅ ?

### ሀ. በየጊዜው የሚደረግ ክፍያ

ሁለቱ ወገኖች የአረቦን ክፍያ የሚደረገው በየጊዜው ሆኖ በየተወሰነ ቀን ነው ብለው ሊስማሙ ይችላሉ ። ኢንሹራንስ ገቢው ክፍያውን በወቅቱ ሳይ ከፍል ቢቀር የኢንሹራንሱ ውል ወዲያውኑ አይቋረጥም ፤ ምክንያቱም የውሉ መጨረሻ ጊዜ ባለመድረሱ ኢንሹራንስ ገቢው ክፍያውን በተወሰነ ጊዜ ውስጥ እንዲያጠናቅቅ እድል ይሰጠዋል ።

የንግድ ሕግ ቁ. 666 በሥራ ላይ ሊውል የሚችለው ኢንሹራንስ ገቢው በየ ጊዜው ሊከፍለው የተዋዋለውን ክፍያ የውሉ ጊዜ ከማለቁ በፊት ያቋረጠ

እንደሆነ ይመስላል ። በዚህ ዓይነት ሁኔታ የአረቦን ክፍያው በየጊዜው በየተወሰነ ቀን የሚከፈል ሲሆን ፤ ክፍያው በዚያ በተወሰነ ቀን ባለመደረጉ ምክንያት ውሉ አይቋረጥም ። ኢንሹራንስ ሰጪው የአረቦን ክፍያው እንዲደረግ ይጠይቃል ፤ ውሉም የሚታገደው ኢንሹራንስ ሰጪው ክፍያውን እንዲፈጽም ከጠየቀ ከአንድ ወር በኋላ ነው ።

## ለ. ውሉን ለማሳደስ የሚደረግ ክፍያ

በልምድ እንደሚታየው ከሆነ የውሉ ማለቂያ ጊዜ ሲደርስ ኢንሹራንስ ሰጪው ለኢንሹራንስ ገቢው የውል ማሳደሻው ክፍያ ጊዜ መቃረቡን የሚያመለክት ማስጠንቀቂያ ይልክለታል ። ይህም በኢንሹራንስ ሰጪው በኩል ውሉ እንዲታደስ እንደቀረበ ሀሳብ ሊቆጠር የሚችል ሲሆን እድሳቱ ያው በፊተኛው ውል አኳኋን ወይም በማስጠንቀቂያው ውስጥ (ለምሳሌም የአረቦኑ ክፍ ማለት ወይም ሌሎች ግዴታዎች ተጨምረውበት ወይም ተቀንሰው) ተሻሽሎ በቀረበ አኳኋን ሊሆን ይችላል ።

በንግድ ሕጉ ውስጥ ኢንሹራንስን የሚመለከቱ ድንጋጌዎች የኢንሹራንስ ፖሊሲ እንዴት እንደሚታደስና የእድሳቱም የሕግ ውጤት ምን እንደሆነ ለይተው አይናገሩም ። ታዲያ ሌሎቹን የንግድ ሕግ ድንጋጌዎች በተመሳሳይ ለኢንሹራንስ ውል እድሳትም ተፈጻሚነት እንዲኖራቸው ለማድረግ ይቻል ይሆን ?

በንግድ ሕጉ ውስጥ ኢንሹራንስን የሚመለከቱት ድንጋጌዎች የሚናገሩት የኢንሹራንስ ውል እንዴት ተፈጻሚነት እንደሚኖረው (ቁ. 659) ፤ በየጊዜው መከፈል የነበረበት አረቦን ሲቋረጥ ደግሞ እንዴት ውሉ እንደሚታገድ ፤ አረቦኑ ከተከፈለ በኋላ ደግሞ ታግዶ የነበረውን ውል እንዴት እንደገና ተፈጻሚነት እንደሚኖረውና (ቁ. 666) በተለየ ሁኔታ የሕይወት ኢንሹራንስ ፖሊሲንእንዴት መልሶ መግዛት እንደሚቻል ነው (ቁ. 710) ። እነዚህ የሕግ ድንጋጌዎች ሁሉ የሚናገሩት ስለአረቦን ክፍያ እንጂ የውሉ ጊዜ ካለቀ በኋላ ምን መደረግ እንዳለበት ስላልሆነ ለውሉ እድሳትም ተፈጻሚነት እንደሚኖራቸው አድርጐ መውሰድ ትክክል አይደለም ።

አንድ ውል የሚፈጸመው በስምምነቱ መሠረት ሥራ ላይ ሲውል ወይንም ደግሞ ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ተፈጻሚነቱ ያበቃል የሚል ግልጽ ስምምነት ሲኖር ነው (ቁ. 1807 ፍትሐ ብሔር ሕግ)። አንዴ ውሉ ከቀረ በኋላ ግን ሁለተኛ ተፈጻሚነት ሊኖረው አይችልም ። ሁለቱ ወገኖች ውሉ የሚታደሰው አረቦን ሲከፈል ነው የሚል ስምምነት ላይ ደርሰው ከሆነ ፤ የአረቦኑ በውሉ መሠረት በተወሰነው ጊዜ ወይም በመጠበቂያው ጊዜ ውስጥ ያለመከፈል ውሉን እንዲፈርስ ያደርገዋል ። በቁ. 666 ኢንሹራንስ ገቢው አረቦኑን በተወሰነው ጊዜ ውስጥ ባለመክፈሉ ብቻ ኢንሹራንስ ሰጪው ውሉን ሊያቋርጥበት አይችልም የሚለው ድንጋጌ እዚህ ላይ ተፈጻሚነት የለውም፤ ምክንያቱም ውሉ ራሱ በክፍያው መቋረጥ ምክንያት ፈርሷልና ነው ።

ያም ሆኖ ቁ. 666 ብዙውን ጊዜ የተለያየ አተረጓጐም ተሰጥቶታል ። በአንዳንድ ጉዳዮች ላይ እንደታየው ፍ/ቤቶች ግልጽ የሆነውን የሕግ ድንጋጌ በመቀበል ውሉ የሚያበቃው በስምምነት በተወሰነው ቀን ነው የሚለውን የሕጉን አነጋገር እንዳለ በሥራ ላይ አውለውታል ። በሌላ ጊዜ ደግሞ ቁ. 666/3/ንና/4/ን የፈረሰውን ውል እንደገና ተፈጻሚነት እንዲኖረው

በማድረግ ተጠቅመውበታል ። የዚህ ነጥብ አከራካሪነት ከዚህ በታች በተ ገለጹት ጉዳዮች ውስጥ ጐልቶ ይታያል ። ዲንሳ ለጴሳና ጥቁር አባይ ኢን ሹራንስ ኩባንያ[5] በተከራከሩበት ጉዳይ ውስጥ ፤ ከሳሽ እ.አ.አ. በኤፕሪል 1969 ዓ. ም. ለግል መኪናው የኢንሹራንስ ውል ከጥቁር ዓባይ የኢንሹራ ንስ ኩባንያ ጋር ተዋውሎ እስከ ሚይ አንድ 1972 ዓ. ም. ድረስ ውሉን እያሳደሰ ይቆያል ። የኢንሹራንስ ገቢው መኪና ሜይ 8/1972 ዓ. ም. ማለ ትም የፊተኛው ውል ቀሪ በሆነ በሰባተኛው ቀን በአደጋ ምክንያት ጉዳት ይደርስበታል ። ኢንሹራንስ ገቢው ይህንኑ ለኢንሹራንስ ኩባንያው አስ ታውቆ ካሣ እንዲከፈለው ይጠይቃል ። ኩባንያውም አደጋው የደረሰው የውሉ ጊዜ ካለቀ በኋላ ስለሆነ ኃላፊነት የለብኝም ብሎ ጥያቄውን ሳይቀ በል ይቀራል ። ከሳሽም ጉዳዩን በግልግል ዳኞች ለመጨረስ ጥረት አድርጐ ስላልተሳካለት በከፍ/ፍ/ቤት ኢንሹራንስ ሰጪውን ድርጅት ይከሰዋል ። ፍ/ቤቱም አደጋው የደረሰው የውሉ ጊዜ ካለቀ በኋላ ስለሆነ ተፈጻሚነት በሌለው ውል ላይ ተመስርቶ ክስ ማቅረብ አይቻልም ብሎ በማተት ለተከሳሹ ኩባ ንያ ይፈርዳል ። ጉዳዩ በይግባኝ ጠ/ፍ/ቤት ደርሶ ፍርዱ እንዲሻር ተደርጓል ። ፍ/ቤቱ በዚሁ ጊዜ በሰጠው ሐተታ ላይ ምንም እንኳን በውሉ መሠረት የተወ ሰነው ጊዜ ቢያልቅም ኢንሹራንስ ሰጪው በመጀመሪያ የኢንሹራንሱ ጊዜ ማለ ቁን አስታውቆ ውሉን ቀሪ ከማድረጉ በፊት ሌላ አንድ ወር የመጠበቅ ሕጋዊ ግዴታ ነበረበት ብሏል ( ቁ. 666/3/ና/4 ) ። ፍ/ቤቱ ሐተታውን በመቀጠል የመጀመሪያው ውል ካለቀ ገና አንደኛው ሳምንት ማለፉ ስለሆነና ክፍያ እንዲ ደረግ ከተጠየቀበት ጊዜ አንስቶ አንድ ወር የመጠበቂያ ጊዜ ስለነበረ ከሳሽ የመ ጠየቅ መብቱ የተጠበቀ ነው ብሏል ።

ይህ ውሳኔ በተመሳሳይ ጉዳዮች ላይ ለዚህ ዓይነት አተረጓጐም መንገድ ይከፍ ታል የሚለው ፍራቻ በኢንሹራንስ ሰጪዎችና በሕግ ባለሙያዎች ዘንድ ትልቅ ሥጋት ፈጥሮ ነበር ። በነዚህ ሰዎች አስተያየት ውሳኔው የኢንሹራንስ ውሎችን ዋጋ የሚያሳጣና ውሉ ካበቃም በኋላ ሊኖረው የሚገባውን ውጤት የሚለውጥ ነው ።

በፍት/ሕ/ቁ. 1806 መሠረት አንድ የውል ግዴታ በውሉ መሠረት ከተፈ ጸመ ቀሪ ይሆናል ። በኢንሹራንስ ውል ከሆነ ደግሞ ውሉ ተፈጻሚነት የሚኖረው በስምምነት እስከተወሰነው ቀን ድረስ ብቻ እንጂ ከዚያ በኋላ አይደለም ።

በዋኬኔ ፈልዳሶና በጥቁር ዓባይ ኢንሹራንስ[6] ክርክር አቶ ዋኬኔ ለሱቁ ጁን 13/1970 ዓ. ም. የእሳትና የሙብረቅ ኢንሹራንስ ገባለት ። ሱቁ ባልታወቀ ምክንያት ጁን 13/1971 ዓ. ም. በእሳት ይቃጠላል ። በውስጡም ከነበሩት ዕቃዎች መካከል አብዛኞቹ ይጋያሉ ። በቃጠሎው ማግስት ኢንሹራንስ ሰጪው የአደጋ ማስታወቂያ ይደርሰዋል ። ሆኖም ኢንሹራንስ ሰጪው አደጋው የደረሰው ውሉ ቀሪ ከሆነ በኋላ ስለሆነ ኃላፊነቱ አይመለከተኝም ይላል ።

ለዚህም የኢንሹራንሱ ውል ተፈጻሚነት ሊኖረው ይችል የነበረው በኢን ሹራንስ ፖሊሲ ውስጥ እንደተጠቀሰው ከጁን 13/1970 ዓ. ም. እስከ ጁን 13/1771 ዓ.ም. አስር ሰዓት ድረስ ሲሆን አደጋው ግን የደረሰው ጁን 13/1971 ዓ. ም. ከምሽቱ አንድ ሰዓት ተኩል ነው ። በከፍ/ፍ/ቤት ውሳኔ መሠረት ኢንሹራንስ ገቢው ከአደጋው ጥቂት ሰዓቶች ቀደም ብሎ ዕቃውን ከሱቁ

ውስጥ ማውጣቱ ስለተደረሰበት ቃጠሎው ካሣ ለማግኘት ሲባል ሆን ብሎ በከሳሹ የተደረገ ስለሆነ ካሣ መጠየቅ አይችልም ሲል ወሰነ ። ጠ/ፍ/ቤት ጉዳዩን በይግባኝ ሰሚነት ተመልክቶ ሁለቱን ወገኖች ካከራከረ በኋላ በሌላ ምክንያት ለተከሳሹ ኩባንያ ፈርዷል ። ፍ/ቤቱ ትኩረት የሰጠው ጭብጥ አንድ የኢንሹራንስ ውል የውሉ ጊዜ አልቆ ቀሪ ከሆነ በኋላ ካሣ ሊጠየቅ በት ይችላል ወይንስ አይችልም የሚለው ነበር ። አደጋው የደረሰው ጁን 13/1971 ዓ.ም. ከምሽቱ በአንድ ሰዓት ተኩል ሲሆን በኢንሹራንስ ውል የተሸፈነው ጊዜ ደግሞ እስከ ጁን 13/1971 ዓ.ም. ከሰዓት በኋላ አስር ሰዓት ድረስ ብቻ ነው ። የኢንሹራንሱ ውል ከዚህ እንደሚከተለው ይነበባል[7] ። «በዚህ የኢንሹራስ ውል ውስጥ እንደራሱ እንደውሉ የሚቆጠሩ የተጻፉት ወይም ተጨምረው የገቡ ድንጋጌዎችና ቅድመ ሁኔታዎች እንደተጠበቁ ሆነው በዚህ ውል ሠንጠረዥ ውስጥ የተጠቀሰው ንብረት ወይም ከፊሉ አረቦን ከተከፈለ በኋላ በሠንጠረዥ ውስጥ ከተወሰነው የጊዜ ገደብ የመጨረሻ ዕለት ከቀኑ አስር ሰዓት በፊት ወይንም ከዚያ በኋላ ከሆነ ደግሞ ኢንሹራንስ ገቢው የውል ማሳደሻ አረቦን ከፍሎ ኮርፖሬሽኑም ተቀብሎት ከሆነ ይህ ንብረት በእሳት ወይንም በመብረቅ አደጋ ቢወድም ወይንም ጉዳት ቢደርስበት ኮርፖሬሽኑ ለኢንሹራንስ ገቢው አደጋው በደረሰ ዕለት ንብረቱ ያወጣው የነበረውን ዋጋ ወይንም በደረሰው ጉዳት መጠን ክፍያ ያደርጋል ወይንም በራሱ ምርጫ ንብረቱን በሙሉ ወይንም በከፊል መልሶ ያቋቁማል ወይንም ይተካል ።»

ከዚህ በላይ ባለው ሁኔታ መሠረት ጠቅላይ ፍ/ቤት ቃጠሎው የደረሰው በኢንሹራንስ ውል የተሸፈነው ጊዜ ካበቃ በኋላ ስለሆነ ኢንሹራንስ ገቢው በውሉ መሠረት ካሣ ሊጠይቅ አይችልም በማለት ወሰነ ።

## 2. ስለ ይርጋ

ሌላው ከዚሁ ጋር አግባብ ያለውና መመርመር ያለበት ጉዳይ የይርጋ ነገር ነው ። ይህን ድንጋጌ በንግድ ሕጉ ውስጥ መጨመር ያስፈለገበት ምክንያት በኢንሹራንስ ውል ውስጥ የሚጨመሩ የውል ቃሎች የኢንሹራንስ ገቢዎች መብት እንዳይገፉ ለመከላከል ነው ። የድንገተኛ አደጋ ኢንሹራንስ ውል ሁኔታ ቁ. 4 የሚከተለውን ይላል ፤

> « … … … ኮርፖሬሽኑ በዚህ ውል ውስጥ በተጠቀሰው መሠረት ካሣ ሲጠየቅ ጥያቄውን ካልተቀበለና ይህ ጥያቄ ተቀባይነትን ባጣ በስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ በዚህ ውል ውስጥ በተደነገገው መሠረት ጉዳዩ ለግልግል ካልቀረበ ጥያቄው እንደተተወ ተቆጥሮ ከዚያ በኋላ በዚህ ውል ላይ የተመሠረተ ማንኛውም ዓይነት የካሣ ጥያቄ አያነሳም[9] ።»

ይህ ሁኔታ (ኮንዲሽን) የኢትዮጵያን የሕግ ድንጋጌዎች እንዲከተሉ ምንም ጥረት ሳይደረግ በእንግሊዝ አገር ከሚሠራባቸው የኢንሹራንስ ፖሊሲዎች በቀጥታ ለተገለበጡ ሁኔታዎች እንደ ጥሩ ምሳሌ ያገለግላል ።

በንግድ ሕግ ቁ. 674/1/[10] መሠረት በኢትዮጵያ ውስጥ ኢንሹራንስን የሚመለከት ክስ የማቅረቢያው የጊዜ ገደብ አደጋው ከደረሰበት ወይንም ተዋዋዮቹ ወገኖች የአደጋውን መድረስ ካወቁበት ጊዜ አንስቶ ሁለት ዓመት ነው ። እንዲህ ማለት ግን የይርጋው ጊዜ በመካከሉ ቢቋረጥም የጊዜ ገደቡ ሁለት ዓመት እንደሆን ይቀራል ማለት አይደለም ። በፍት/ሕግ ቁ. 1852/1/ መሠረት የይርጋው

ጊዜ በተቋረጠ ቁጥር አዲስ የይርጋ ዘመን መቆጠር ይጀምራል ። የኢንሹራንሱ ውል ስለይርጋው ጊዜ መቋረጥ ምንም ሳይናገር የጊዜ ገደቡን ብቻ ወደ ስድስት ወራት ዝቅ ያደርገዋል ። በድንገተኛ አደጋ የኢንሹራንስ ፖሊሲ ሁኔታ ቁ.3 ውስጥ የአደጋው ማስታወቂያ በሶስት ወራት ጊዜ ውስጥ ለኮርፖሬሽኑ ካልደረሰ ኮርፖሬሽኑ ለማንኛውም የካሣ ጥያቄ ኃላፊነት እንደሌለበት ይገልጻል ። ይህን ማለት አደጋው ስለመድረሱ ከሶስት ወራት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ የአደጋው ማስታወቂያ ለመድን ድርጅቱ መድረስ አለበት ፤ ያለዚያ ድርጅቱ በኃላፊነት አልጠየቅም ይላል ።

በንግድ ሕግ ቁ. 670 መሠረት የኢንሹራንስ ገቢው ከአቅም በላይ በሆነ ኃይል ምክንያት ካልሆነ በስተቀር ማንኛውም ኢንሹራንስ ሰጪውን በኃላፊነት ሊያስጠይቅ የሚችል አደጋ ሲደርስ ወዲያውኑ አደጋው መድረሱን እንዳወቀ ወይንም በአምስት ቀናት ውስጥ ለኢንሹራንስ ሰጪው ያስታውቃል ይላል ። የንግድ ሕግ ቁ. 670 የአደጋ ማስታወቂያውን ጊዜ በኢንሹራንስ ውል ውስጥ ከተሰጠው ጊዜ ይልቅ ያሳንሰዋል ። በሌላ በኩል ደግሞ የኢንሹራንስ ፖሊሲ ድንጋጌና የንግድ ሕግ ቁ. 670 በንግድ ሕግ ቁ. 674 ከተሰጠው የይርጋ ጊዜ ጋር ይቃረናሉ ።

በቁ. 674/1/ መሠረት ኢንሹራንስ ሰጪውን ለአደጋው ተጠያቂ ማድረግ የሚቻለው አደጋው በደረሰ በሁለት ዓመታት ጊዜ ውስጥ ነው ። ከዚህም ይልቅ በቁ. 674/3/ ሥር እንደተጻፈው ተዋዋይ ወገኖች በፈቃዳቸው ይህንን የጊዜ ገደብ ከዚህ አሳንሰው መስማማት እንደማይችሉ በግልጽ የተደነገገ ሲሆን ይህም ሕግ አውጪው ለዚህ ጉዳይ ምን ያህል ክብደት እንደሰጠው ያመለክታል ። ይህን የይርጋንና የአደጋ ማስታወቂያ ጊዜን የሚመለከት አንድ ፍ/ቤት ደርሶ ውሳኔ የተሰጠበት ጉዳይ አለ ። ይኸውም ወ/ሮ ቅድስት ሚቸል ኮትስ ኩባንያን የከሰሱበት ነው ። አቶ ጌታሁን የተባሉ የወ/ሮ ቅድስት ባል ከኩባንያው የኢንሹራንስ ክፍል የአደጋ ኢንሹራንስ ፖሊሲ ይገዛሉ ። በውሉ ስምምነት መሠረት ኢንሹራንስ ገቢው ቢሞቱ ወይንም አደጋ ቢደርስባቸው 40'000 ብር ካሣ ይከፍላቸዋል ። አቶ ጌታሁን መኪና እየነዱ ወደ ጂማ ሲሄዱ ጃኑዋሪ 5/1967 ዓ.ም. ከባድ አደጋ ስላጋጠማቸው በዚሁ ጠንቅ ጃንዋሪ 23/1967 ዓ.ም. ከዚህ ዓለም በሞት ይለያሉ ። ስለአደጋው መድረስና ሟችም የሞቱት በዚሁ የመኪና አደጋ ጠንቅ መሆኑን የሚያመለክት ማስረጃ ጨምሮ የአደጋ ማስታወቂያው ጃንዋሪ 26/1967 ዓ.ም. ለኩባንያው ይደርሳል ። ኩባንያው ግን በፖሊሲው ሁኔታ ቁ.2 መሠረት የጽሑፍ ማስታወቂያው አደጋው በደረሰ ወይንም ሕመሙ ከጀመረበት ቀን አንስቶ በ14 ቀናት ውስጥ ለኩባንያው መድረስ ስለሚኖርበትና ይህ ደግሞ ባለ መደረጉ ኃላፊነቱን እንደማይቀበል ገለጸ ። ባሁኑ ጉዳይ ውስጥ የአደጋው ማስ ታወቂያ የደረሰው በ21ኛው ቀን ላይ ነበር ። ይህም ማለት ከጃንዋሪ 5 ቀን 1967 ዓ.ም. እስከ ጃንዋሪ 26 ቀን 1967 ዓ.ም. ድረስ የነበረው ጊዜ ማለት ነው ። ከፍተኛው ፍ/ቤት ማስታወቂያው በ14 ቀናት ውስጥ መድረስ አለበት ተብሎ በፖሊሲው ላይ የተሰጠውን የጊዜ ገደብ ሁኔታ ላይ ትኩረት በማድረግ ለተከሳሹ ፈረደ ። ጉዳዩ በይግባኝ ጠ/ፍ/ቤት ደርሶ ፍ/ቤቱ ጉዳዩን ከመረመረ በኋላ ይህ ሁኔታ የተደነገገው በአደጋ ምክንያት ለቆሰሉ ወይንም ለታመሙ ሰዎች እንጂ በአደ ጋው ለሞቱ ሰዎች አይሠራም በማለት ወሰናል ። ሆኖም ሁለቱም ፍ/ቤቶች ቢሆኑ ውሳኔያቸውን የሰጡት በትክክለኛው የንግድ ሕግ ድንጋጌዎች መሠረት አይደለም ። ሌላው ከዚሁ ጋር ተመሳሳይነት ያለውና በሕጉና በተለያዩ ፖሊ ሲዎች መካከል ያሉትን ግልጽ ልዩነቶች የሚያመለክተው በመካን እየሱስ ቤተ

ክርስቲያንና በኢት/መድን ድርጅት መካከል የተነሳው ክርክር ነበር[110] ። በሞ ራኒ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ኩባንያና (ውል ተቀባይ) በአፍሪካ አንድነት ኢን ሹራንስ መካከል ዲሴምበር 16/74 ውል ተፈረመ ። ይኸውም ውል የሥራ ክን ውን ዋስትና (ፐርፎርማንስ ቦንድ) ሲሆን የኢንሹራንስ ድርጅቱ ለኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን ውል ተቀባዩ በውሉ መሠረት ግዴታውን ባይወጣ እስከ 200,000 ብር ለመክፈል ዋስትና የገባበት ነው ።

ውል ተቀባይ የሕንጻውን ሥራ ከጀመረ በኋላ በድንገት ኢትዮጵያን ለቅቆ በመሄዱ የሕንጻው ሥራ እንደተቋረጠ ለዋቂት ወራት ቆየ ። ውል ተቀባዩ የጀ መረውን ሥራ ተመልሶ እንደማያጠናቅቅ አሠሪው አንዳንድ ፍንጮችን ካገኘ በኋላ ይህንኑ ለኢንሹራንስ ኩባንያው አስታውቆ በሥራው መቋረጥ ምክንያት የደረሰበትን ጉዳት እንዲካስ ጠየቀ ። የመድን ድርጅቱም በሚከተሉት ምክን ያቶች ኃላፊነቱን እንደማይቀበል ለግልግል ኮሚቴው አስታወቀ ፤

ሀ. ውል ሰጪው በፖሊሲ ቁ. 1 መሠረት በአጭር ጊዜ ውስጥ ስለሁኔታው ለኢ ንሹራንስ ድርጅቱ ማስታወቂያ አልላከም ። ከዚህም ሌላ ውል ተቀባዩ አገ ሪቱን ለቅቆ የወጣው ከጁን 1975 ዓ.ም. በፊት ሲሆን ማስታወቂያው ግን ለኢንሹራንስ ኩባንያው የደረሰው በኖቬምበር 1976 ዓ.ም. መሆኑን አን ስቶ ኩባንያው ተከራከረ ።

ለ. ውል ሰጪ በፖሊሲው ቁ.4 መሠረት የጉዳዩ የይርጋ ጊዜ ውል ተቀባይ በውሉ መሠረት ግዴታውን ሳይፈጽም ከቀረበት ጊዜ እንስቶ እስከ 12ኛው ወር ብቻ በመሆኑና ግን አሁን ይህ ክስ የቀረበው ከሳሽ ስለሁኔታው ባወቀ በ16ኛው ወር በመሆኑ ልጠየቅ አይገባም አለ ።
እዚህ ላይ ሁለት ሊታረቁ የማይችሉ ሀሳቦች ይነሳሉ ።

1. በሥራ ክንውን ዋስትና ፖሊሲ ድንጋጌ ቁ. 1 መሠረት ማንኛውም የኢን ሹራንስ ገቢ ጉዳት የሚያስከትል ሁኔታ መድረሱን ሲያውቅ ወዲያውኑ ለድርጅቱ ማሳወቅ አለበት ። የአደጋ ፖሊሲ ቁ.2 (በወ/ሮ ቅድስትና በሚ ችል ኮትስ ክርክር ውስጥ እንዳየነው) የካሣ ጥያቄ ሊነሳ የሚችልበትን ጊዜ በግ ልጽ ይናገራል ። ይኸውም አደጋው በደረሰ ወይንም ሕመሙ በጀመረ በ14 ቀናት ውስጥ ማስታወቂያው በጽሑፍ ለኢንሹራንስ ድርጅት መድረስ አለበት የሚለው ነው ። አንዱ የኢንሹራንስ ውል ድንጋጌ ማስታወቂያው በአጭር ጊዜ ውስጥ መድረስ አለበት ሲል ፤ ሌላው ደግሞ ማስታወቂያው በስንት ጊዜ ውስጥ መድረስ እንደሚገባው ቁርጥ አድርጐ ይደነግጋል ። በፊተኛው ሁኔታ «በአጭር ጊዜ ውስጥ» የሚለው አነጋገር የተለያየ እተ ረጓጐም ሊያስነሳ የሚችል ነው ። ይህ እንግዲህ በተለያዩ የኢንሹራንስ ፖሊሲዎች መካከል እንኳን የማይጣጣሙ ድንጋጌዎች መኖራቸውን ለማ ሳየት የቀረበ ነው ። ይህም ማለት አንዳንዶቹ ፖሊሲዎች የሚሰጡት የጊዜ ገደብ አሻሚ ሲሆን የአንዳንዶቹ ደግሞ ቁርጥ ያለ ነው ።

2. በሥራ ክንውን ዋስትና ፖሊሲ ሁኔታ ቁ.4 ውስጥ እንደተጻፈው በውሉ ላይ የተመሠረተ የክፍያ ክስ ለክሱ ምክንያት የሆነው ሁኔታ መኖሩ በታወቀ በ12 ወራት ጊዜ ውስጥ ካልተጀመረ በስተቀር በድርጅቱ ላይ ሊቀርብ አይችልም ።

ይህ ድንጋጌ በኢንሹራንስ ውል ላይ የተመሠረተ ክስ ሊቀርብ የሚችለው ፤ ለክሱ መነሻ የሆነው ነገር በተፈጠረ በሁለት ዓመታት ውስጥ ነው ተብሎ

በንግድ ሕግ ቁ. 674/1/ የተወሰነውን የይርጋ ጊዜ የሚጻረር ነው ። ይህ ደግሞ ከኢትዮጵያ ሕግ ጋር እንዲስማሙ ለማድረግ ምንም የማሻሻያ ጥረት ሳይደረግባቸው በእንግሊዝ አገር የሚሠራባቸው ፖሊሲዎች እዚህ በሥራ ላይ የመዋላቸው አንዱ ሌላ ምሳሌ ነው ።

3. እውነተኛ ነገሮችን ስለመሸሸግ

የኢትዮጵያ የንግድ ሕግ አስፈላጊ ነገሮች ኢንሹራንስ በገባው ሰው ስለሚሸሸጉበትም ሁኔታ መጠነኛ ድንጋጌዎች ይዟል[11] ። የኢትዮጵያ ሕግ ምን ጊዜም ቢሆን «ከፍተኛ ቅን ልቦና» የሚለውን መርህ ይከተላል ። ይህ ከፍተኛ ቅን ልቦና መኖር ያለበት አደጋው ከመድረሱ ቦፊት ብቻ ሳይሆን ከደረሰም በኋላ ነው ። በመሠረቱ አደጋ በመድረሱ ጉዳት የደረሰበት አንድ ኢንሹራንስ ገቢ በውሉ መሠረት እንዲፈጸምለት ክስ በሚያቀርብበት ጊዜ ውሉ በተፈጸመበት (ፖሊሲው በተጻፈበት) ጊዜ የአደጋውን ባሕርይ ወይም መጠን የሚያሳየውን ወይም ውሉን ከመፈጸም ያግደው የነበረውን ወይም መክፈል ይገባው የነበረውን የኢንሹራንስ መግቢያ ገንዘብ መጠን ያፋልስ የነበረውን ማንኛውንም ነገር በትክክልና በሙሉ አልገለጽክም የሚል መከላከያ ሊቀርብበት እንደሚችል መገንዘብ አለበት ።

በአጠቃላይ አነጋገር በኢትዮጵያ ሕግ ቅን ልቡናን መጣስ በውሉ መጽናት ላይ በሚያስከትለው የተለያየ ውጤት መሠረት በሶስት ተመድቧል ። እነርሱም ፤

ሀ. <u>መሸሸግ፡</u>— ይህ እያወቁ እውነቱን ነገር በመሸሸግ የሚፈጸመውን የቅን ልቡና መጣስ ይመለከታል ።

ለ. <u>በቅን ልቡና ትክክል ያልሆነ ነገር መናገር፡</u>— ይህ ሆነ ተብሎ ሳይሆን ወይም ያለአንዳች አጭበርባሪነት የሚነገረውን ትክክለኛ ያልሆነ አባባል ይመለከታል ።

ሐ. <u>አታላይነት</u> ፤ ይህ አንድ ነገር ሀሰት መሆኑን እያወቁ ሀሰቱን እውነት አስመስሎ ማቅረብን ይመለከታል ። ነገር ግን ጉዳዩን ለመመርመር ሲባል ባለመጠንቀቅ የተነገረው ሀሰት ነገር አይደለም[12]

በንግድ ሕግ ቁጥር 668/1/ መሠረት ኢንሹራንስ የገባው ሰው እያወቀ እውነቱን ነገር የሸሸገ ወይም የሀሰት መግለጫ የሰጠ እንደሆነ ፤ እውነተኛው ነገር ተገልጾለት ቢሆን ኖሮ ኢንሹራንስ ሰጪው ይህን ውል አይዋዋልም ፤ ወይም ተጠቃሚው ከፍ ያለ ገንዘብ እንዲከፍል የሚያደርግበት ውል ይዋዋል ነበር እስከሚያሰኝ ድረስ እነዚህ የተሸሸጉ ነገሮች ወይም በሀሰት የተሰጡ መግለጫዎች የኢንሹራንስ ሰጪውን የአደጋውን አስተያየት ለውጠውበት እንደሆነ ፤ ውሉ ፍርስ ይሆናል ። ነገር ግን ሕጉ የሀሰት መግለጫው ሆን ተብሎ የማይደረግበትን ሁኔታም ይደነግጋል ። መሸሸጉ ወይም የሀሰት መግለጫው በቅን ልቡና የተደረገ እንደሆነና የታወቀውም አደጋው ከመድረሱ በፊት የሆነ እንደሆነ ፤ ኢንሹራንስ ሰጪው ሁለት ምርጫ ተሰጥቶታል ፤ ይኸውም ለኢንሹራንስ ገቢው ማስታወቂያ ከሰጠ ከአንድ ወር በኋላ ውሉን የማፍረስ ወይም የኢንሹራንስ መግቢያው ገንዘብ ተጨምሮ ውሉ እንዲቀጥል የማድረግ[13]። ነገር ግን የተሸሸገው ነገር የታወቀው አደጋው ከደረሰ በኋላ የሆነ እንደሆነ ለኢንሹራንስ ገቢው

የሚከፈለው ገንዘብ መጠን ይቀነሳል በማለት ሕጉ ይደነግጋል[14] ። ሆኖም በፖሊሲው ላይ የተገለጸው ሁኔታ በሕጉ ከተደነገገው ለየት ያለ አዝማሚያ ይታይበታል ። በአጠቃላይ አደጋ ፖሊሲ ቁጥር 8 የተጠቀሰው ሁኔታ እንዲህ ይላል ፤ « ... ... ... ... ኢንሹራንስ ገቢው አስቀድሞ በሚያቀርበው ጥያቄ ወይም ይህን ኢንሹራንስ በሚያድስበት ጊዜ በሰጠው ቃል ወይም ከዚህ ውል ጋር በተያያዘ ጉዳይ በሚቀርብ ክርክር ሀሰቱን እውነት አስመስሎ ያቀረበ እን ደሆነ ወይም ሆነ ብሎ ሁኔታውን አጋንኖ ያቀረበ እንደሆነ ወይም ሆነ ብሎ መግለጽ ይገባው የነበረውን ነገር ሳይገልጽ የቀረ እንደሆነ ፖሊሲው ዋጋ ከማ ጣቱም በላይ የተከፈለው የኢንሹራንስ መግቢያ ገንዘብ አይመለስም[15]። » በመሆኑም እንደ ፖሊሲው አባባል በኢንሹራንስ ገቢው ሊገለጽ የሚገባው ነገር የተሸሸገ ወይም የሀሰት መግለጫ የተደረገ እንደሆነ ፖሊሲውን ዋጋ ያሳጣዋል ፤ ኢንሹራንስ ገቢው የከፈለውን የኢንሹራንስ መግቢያ ገንዘብም ያጣል ። በአ ጠቃላይ አነጋገር ፖሊሲውና የሕጉ ድንጋጌዎች ኢንሹራንስ ገቢው ሊደርስ የሚ ችለውን አደጋ ባሕርይና መጠን የሚያሳየውን ውል ከመዋዋል ሊያግድ የሚ ችለውን ወይም የኢንሹራንስ መግቢያውን ገንዘብ ተመን ሊለውጥ የሚችለውን ማንኛውንም ነገር በትክክል መግለጽ እንዳለበት በኢንሹራንስ ገቢው ላይ ግዴታ ይጥልበታል።ይሁን እንጂ ይህ የመሸሸግ ወይም አንድን ነገር አለመግለጽ በሚያ ስከትለው ውጤት ረገድ በንግድ ሕግና በፖሊሲው መካከል የሚታዩትን ዋና ዋና ልዩነቶች ሊሰውራቸው አይችልም ። ባጭሩ እንደሚከተለው ማሳየት ይቻ ላል ።

## <u>በኢንሹራንስ ገቢው እውነተኛ የሆነው ነገር ሲሸሸግ በሕጉና በፖሊሲው የሚያስከትለው ውጤት</u>

| | |
|---|---|
| ሀ. 1. መሸሸጉ ሆነ ተብሎ በሚደረግበት ጊዜ | <u>በንግድ ሕግ የሚያስከትለው ውጤት</u> ፤<br>ውሉ በኢንሹራንስ ሰጪው ይቋ ረጣል ፤ ኢንሹራንስ ሰጪው የኢንሹራንስ መግቢያውን ገን ዘብ ያስቀራል ። |
| 2. መሸሸጉ በቅን ልቡና በሚሆ ንበት ጊዜ | |
| ሀ/ መሸሸጉ ከአደጋው በፊት በኢንሹራንስ ሰጪው ሲታ ወቅ | ከአንድ ወር ማስጠንቀቂያ በኋላ ውሉን ማፍረስ ወይም የኢንሹራንስ መግቢያውን ገን ዘብ መጨመርና ውሉን መቀ ጠል ። |
| ለ/ መሸሸጉ ከአደጋው በኋላ ሲታወቅ | ሊደርስ የሚችለውን አደጋ በሙሉና በትክክል ተገልጾ ቢሆን ኖሮ ለኢንሹራንስ ሊከ ፈል ይገባ የነበረውን በማመ ዛዘን ኪሣራውን በዚሁ መጠን መቀነስ ። |

| | | |
|---|---|---|
| ለ. | በጥያቄ የሀሰት መግለጫ ማቅረብ ፤<br>ሆን ተብሎ የተጋነነ ነገር ማቅረብ ወይም ሆን ብሎ መተው (አለማድረግ) | በፖሊሲው የሚያስከትለው ውጤት<br>ፖሊሲው ዋጋ ያጣል ፤ የኢንሹራንስ መግቢያው ገንዘብ ለኢንሹራንስ ሰጪው ይቀራል ። |

በሕጉና በፖሊሲው መካከል ያለውን የውጤት ልዩነት ማስተዋል ይቻላል ። እንደ ፖሊሲው አባባል ማናቸውም ሆን ተብሎ የተደረገ ወይም ሆን ተብሎ ያል ተደረገ የሀሰት መግለጫ ፖሊሲውን ዋጋ ያሳጣዋል ፤ በሌላ በኩል ሕጉ ሆን ተብሎ የተደረገ መሸሸግና ሆን ተብሎ ያልተደረገ የሀሰት መግለጫ በማለት ውጤቱን በሁለት ይከፍለዋል። መሸሸጉ ሆን ተብሎ የተደረገ እንደሆነ ውሉ ይፈርሳል ፤ መሸሸጉ የተደረገው በቅንልቡና ከሆነና ይኸው የተገለጸው አደጋው ከመድረሱ በፊት ከሆነ ኢንሹራንስ ሰጪው ሁለት ምርጫ አለው ፤ ይኸውም ከአንድ ወር ማስታወቂያ በኋላ ውሉን ማፍረስ ወይም የኢንሹራንስ መግቢያውን ገንዘብ ጨምሮ ውሉ እንዲቀጥል ማድረግ በማለት ሕጉ ይደነግጋል ። ነገር ግን መሸሸጉ የታወቀው አደጋው ከደረሰ በኋላ ከሆነ ኢንሹራንስ ሰጪው ለኪሳራው የሚከፍለውን ገንዘብ በዚያው መጠን ሊቀንስ ይችላል ። የፍትአብሔር ሕግ ቁጥር 1678 ሁለት ወገኖች የሚዋዋሉት ውል ከሕጉ ዓላማ እስካልራቀና የሕጉን አስገዳጅ ድንጋጌዎች እስካልጣሰ ድረስ ማናቸውንም ውል ለመዋዋል ነፃነት አላቸው በማለት ይደነግጋል ። ይህን ከዚህ ላይ ያነሳነው ፤ ምንም እንኳን ኢንሹራንስ ገቢውና ኢንሹራንስ ሰጪው በማናቸውም ዓይነት ሁኔታ ለመዋዋል ነፃነት ቢኖራቸውም ውላቸው ከሕጉ መንፈስ ሊርቅ ወይም ከሕጉ አስገዳጅ ድንጋጌዎች ውጪ ሊሆን የማይችል መሆኑን ለማሳየት ነው ።

ማክጊልቭሬይ[16] እንዲህ ይላል ፤ «አንድ ነገር አስፈላጊ ነገር ነው ፤ መገለጽ ነበረበት ፤ ብሎ ለመወሰን ኢንሹራንስ ሰጪዎች እውነተኛው ነገር ተገልጾ ቢሆን ይህ የአደጋውን አስተያየት ይለውጥባቸው እንደነበረ ማረጋገጥ አያስፈልጋቸውም ፤ እውነተኛው ነገር ተገልጾ ቢሆን ኖሮ ልምድ ያላቸው ኢንሹራንስ ሰጪዎች ጉዳዩን ላለመቀበል ወይም የኢንሹራንስ መግቢያውን ገንዘብ ለመጨመር ይገፋፉቸው ነበር ብሎ ማረጋገጥ በቂነው። « ኢንሹራንስ ገቢው ኪሣራ እንዲከፈለው በሚጠይቅበት ጊዜና ኢንሹራንስ ሰጪው መሸሸግን በማንሳት በሚቃወምበት ጊዜ ኢንሹራንስ ሰጪው የሚከተሉትን ሁኔታዎች የማረጋገጥ ኃላፊነት አለበት ፤

ሀ/ እውነተኛው ነገር ተሸሽጎ እንደነበር ወይም የሀሰት መግለጫ ተሰጥቶ እንደነበር ፤

ለ/ የተባለው እውነተኛ ነገር አስፈላጊ እንደነበር ፤

3. የተባለው እውነተኛ ነገር አስፈላጊ ለመሆኑና የሐሰት መግለጫ ተሰጥቶ እንደነበር ፍርድ ቤቱ እንዴት እርግጠኛ ሊሆን ይችላል? የኢትዮጵያን የንግድ ሕግ ሕገ—ፍልስፍና አመጣጥ ስንመረምር ከሚከተሉት አንዱ እውነተኛ ነገር (አስፈላጊ ነገር) ሊሆን እንደሚችል እንረዳለን[17] ።

   ሀ. የአደጋውን ባሕርይ ወይም መጠን ሊያሳይ የሚችል ነገር ፤ ወይም

   ለ. ውሉን ከመዋዋል ሊያግድ የሚችል ነገር ፤ ወይም

ሐ. የኢንሹራንስ መግቢያውን ገንዘብ መጠን ሊያቃውስ የሚችል ነገር ። በአጠቃላይ የአንድ ነገር አስፈላጊ መሆን የፍሬ ነገር ጥያቄ ሲሆን ፍርድ ቤቱ ትክክለኛ ከሆነ ውሳኔ ላይ ይደርስ ዘንድ መረጋገጥ ያለበት ልዩ ሙያ ባላቸው ሰዎች ከመሆኑም በላይ ፤ ልምድ ያለው ኢንሹራንስ ሰጪ በሀሰት በተሰጠው መግለጫ ወይም በተሸሸገው እውነተኛ ነገር ምክንያት ስለአደጋው ይኖረው የነበረው አስተያየት ልዩ ይሆን እንደነበር ማረጋገጥ አለበት[18] ። በከሳሽ በወይዘሮ ቅድስት እና በተከሳሽ በሚቻል ኮትስ ኩባንያ ጉዳይ ላይ ፤ ተከሳሽ ያነሰው መከላከያ ኢንሹራንስ ገቢዋ የፖሊሲውን ፎርም በሚሞሉበት ጊዜ እውነተኛውን ነገር ሸሽገዋል ፤ ኢንሹራንስ ሰጪው እውነተኛው ነገር ቢገለጽለት ኖሮ ውሉን ያፈርሰው ነበር ወይም የኢንሹራንስ መግቢያውን ገንዘብ መጠን ያሳድገው ነበር የሚል ነበር ። ይሁን እንጂ ከሳሽ ሳይገልጽ የቀረው ነገር አስፈላጊ ነገር አልነበረም ፤ የውሉን መሠረት ሊያናጋው አይችልም ነበር ፤ ብለው ከመከራከራቸው በቀር ፍርድ ቤቱ ይህን ጉዳይ እንደ ጭብጥ አንስቶ ውሳኔ አልሰጠበትም ። በመሆኑም የፍርድ ቤቱን አቋም ከዚህ ላይ መናገር አይቻልም[19] ።

## 4. የአደጋው እየከበደ መሄድ

የንግድ ሕግ ቁ. 669 ስለ አደጋ እየከበደ መሄድ ይደነግጋል ። እንዲህ ይላል ፤ «ሊደርስ የሚችለው አደጋ እየከበደ መሄድ ውሉ በተደረገ ጊዜ አደጋው በዚህ ሁኔታ እየከበደ የሚሄድ መሆኑ ቢታወቅ ኖሮ ኢንሹራንስ ሰጪው የማይዋዋል መሆኑ ወይም ቢዋዋልም ኢንሹራንስ ገቢውን ከፍ ያለ የኢንሹራንስ መግቢያ ገንዘብ አስከፍሎ ይዋዋል ነበር የሚያሰኝ ሆኖ ሲገኝ ፤ ኢንሹራንስ በገባው ሰው ምክንያት ሲሆን አደጋው እየጨመረ እንዲሄድ ያደረገው ሁኔታ በተደረገ በአሥራ አምስት ቀን ውስጥ ወይም ይህን ድርጊት ኢንሹራንስ ገቢው ካወቀበት ከአሥራ አምስት ቀን በማይበልጥ ጊዜ ውስጥ ኢንሹራንስ ገቢው ለኢንሹራንስ ሰጪው ማስታወቅ አለበት » ። ኢንሹራንስ ሰጪው ውሉን ለማፍረስ ወይም ለኢንሹራንስ የሚከፈለው ገንዘብ ከፍ እንዲልና ውሉ እንደጸና እንዲቆይ ለማድረግ ይችላል ። ይሁን እንጂ በፖሊሲው የተሰጠው የአደጋን መክበድ ያለማስታወቅ ውጤት በሕጉ ከተደነገገው በጭራሽ የተለየ ነው ። የአካል ጉዳት አደጋ ፖሊሲ ፤ ንዑስ ክፍል 3 እንዲህ ይላል ፤ «ኢንሹራንስ ገቢው ድርጅቱን ሳያስታውቅ ፤ ፈቃድ ሳያስገኝና በድርጅቱ ሲጠየቅ ተጨማሪ የኢንሹራንስ መግቢያ ገንዘብ ሳይከፍል ከፍ ያለ አደጋ ሊያስከትል በሚችል ተግባር ላይ የተሰማራ እንደሆነ ይህ ፖሊሲ ፍጹም ዋጋ አይኖረውም ፤ ይህን በሚመለከት ረገድ ማናቸውንም የመብት ጥያቄ ማቅረብ አይቻልም ። » እንደዚህ በመሆኑም ምክንያት የአደጋ መክበድ ያለማስታወቅ ውጤትን በሚመለከት ረገድ በሕጉና በፖሊሲው መካከል ልዩነት እናያለን ። ሊደርስ የሚችል አደጋ እየከበደ የሄደ እንደሆነና ኢንሹራንስ ሰጪው አደጋው እየጨመረ እንዲሄድ ያደረገውን ሁኔታ በተደረገ በአሥራ አምስት ቀን ውስጥ ወይም ይህንን ድርጊት ኢንሹራንስ ገቢው ካወቀበት ከአሥራ አምስት ቀን በማይበልጥበት ጊዜ ውስጥ እንዲያውቅ የተደረገ እንደሆነ ፤ ኢንሹራንስ ሰጪው ውሉን ለማፍረስ ወይም ለኢንሹራንስ የሚከፈለውን ገንዘብ ጨምሮ ውሉ እንዲጸና ለማድረግ ይችላል ። ነገር ግን ማስታወቂያ ያልተሰጠ እንደሆነ፣ ውጤቱ በቁጥር 668 ድንጋጌ መሠረት ይሆናል።

## ሊደርስ የሚችለው አደጋ እየከበደ መሄዱን በኢንሹራንስ ገቢው ያለማስታወቅ (ማለትም በተወሰነው ጊዜ ያለማስታወቅ) በሕጉና በፖሊሲው የሚያስከትለው ውጤት

| | | በንግድ ሕግ ውስጥ ያለው ውጤት[20] |
|---|---|---|
| 1. | ሊደርስ የሚችለውን አደጋ እየከበደ መሄዱን ያለማስታወቅ ሆን ተብሎ የተደረገ ሲሆን | ውሉ በኢንሹራንስ ሰጪው ይፈርሳል ፤ ኢንሹራንስ ሰጪው ለኢንሹራንስ መግቢያ የተከፈለውን ገንዘብ ያስቀራል ። |
| 2. | ሊደርስ የሚችለው አደጋ እየከበደ መሄዱን ያለማስታወቅ በቅን ልቡና የተደረገ ቢሆን | |
| ሀ. | አደጋው ከመድረሱ በፊት የተገለጸ እንደሆን | ከአንድ ወር ማስታወቂያ በኋላ ውሉን ማፍረስ ወይም የኢንሹራንስ መግቢያውን ገንዘብ በመጨመር ውሉ እንዲቀጥል ማድረግ ። |
| ለ. | አደጋው ከደረሰ በኋላ የተገለጸ እንደሆን | ሊደርስ የሚችለው አደጋ በሙሉና በትክክል ተገልጾ ቢሆን ኖሮ ለኢንሹራንስ ሊከፈል ይገባ የነበረውና በአሁኑ ጊዜ በተከፈለው የኢንሹራንስ መግቢያ ገንዘብ መካከል ልዩነት ታይቶ ኢንሹራንስ ገቢው የሚከፈለው ገንዘብ በዚሁ ልክ ተቀናሽ ይሆናል ። |
| | | **በፖሊሲው ውስጥ ያለው ውጤት** |
| 3. | ሊደርስ የሚችለው አደጋ እየከበደ መሄዱን ለድርጅቱ ያለማስታወቅ | ፖሊሲው ፍጹም ዋጋ ያጣል ፤ ይህን በሚመለከት ረገድ የመብት ጥያቄ ማቅረብ አይቻልም ። |

ስለዚህ ሊደርስ የሚችለው አደጋ እየከበደ መሄዱን ያለማስታወቅ በሕጉና በፖሊሲው የሚያስከትለው ውጤት የተለያየ እንደሆነ መመልከት ይቻላል ። ፖሊሲው ሊደርስ የሚችለው አደጋ እየከበደ መሄዱን ባለማስታወቅ በአጠቃላይ ውሉን ፈራሽ ሲያደርገው ፤ ሕጉ ሆን ተብሎ የተደረገና ሆን ተብሎ ያልተደረገ ያለማስታወቅ ብሎ ከሁለት ከመክፈሉም በላይ የሚያስከትለውን ሕጋዊ ውጤትም እንደዚሁ ለያይቶ ይገልጸዋል ።

### 5. የሕይወት ኢንሹራንስ (ፖሊሲ)

የኢንሹራንስ ኩባንያዎች ደንበኞችን ለመሳብ የሚረዱ የውል ቃሎችን በፖሊሲው ውስጥ ያስገባሉ ። የሕይወት ኢንሹራንስ ፖሊሲ ቁጥር 9 ጠቅላላ ድንጋጌ እንዲህ ይላል ፤ «ኢንሹራንስ ገቢው ፖሊሲው ከተፈረመበት ወይም

ከታደሰበት ቀን ጀምሮ በሁለት ዓመት አእምሮው ጉደሎ ሆኖ ወይም ጤነኛ ሆኖ ራሱን የገደለ እንደሆነ የሚከፈለው የኢንሹራንስ ገንዘብ መጠን ከተከፈለው የኢንሹራንስ መግቢያ ገንዘብ መጠን ጋር እኩል ይሆናል ፤ በምንም ዓይነት ከዚህ አይበልጥም ።» ከዚህ ላይ ፖሊሲው የተከፈለው የኢንሹራንስ መግቢያ ገንዘብ በሙሉ ለኢንሹራንስ ገቢው እንደሚመለስለት ይናገራል ፤ በሌላ በኩል ፤ ሕጉ ይህን ጉዳይ ከፋፍሎ ይመለከተዋል ። ቁጥር 699/1/ «ተቃራኒ ስምምነት ቢኖርም እንኳ ለሕይወት የሚደረግ ኢንሹራንስ ፤ ኢንሹራንስ የገባው ሰው ሆን ብሎ ራሱን የገደለ እንደሆነ ኢንሹራንሱ ዋጋ የለውም ... ... ... » ይላል ። በተጨማሪ «ሆን ብሎ ራሱን ያልገደለ መሆኑን ተጠቃሚው ማስረዳት የቻለ እንደሆነ የኢንሹራንሱ ውል ዋጋ ያለው ይሆናል ።» ይላል ። ከዚህ ላይ ራስን መግደል በሕጉና በፖሊሲው የሚያስከትለው ውጤት የተለያየ እንደሆነ እንመለከታለን ። በሕጉ ፤ ራስን መግደል ሆን ተብሎ ያልተደረገ እንደሆነ የኢንሹራንሱ ውል ዋጋ ያለው ይሆናል ። ነገር ግን ራስን መግደሉ ሆን ተብሎ የተደረገ እንደሆነ የኢንሹራንሱ ውል ፍርስ ይሆናል ፤ ካሣም አይከፈልም ። የሕይወት ኢንሹራንስ ፖሊሲ ጠቅላላ ድንጋጌ የኢንሹራንስ መግቢያን ገንዘብ በሚመለከት ረገድም ከሕጉ ጋር የማይታረቅ አቋም አለው ። የሕይወት ኢንሹራንስ ፖሊሲ ቁጥር 2 እንዲህ ይላል ፤ «የኢንሹራንስ መግቢያ ገንዘብ እና በየጊዜው የሚከፈለውን የኢንሹራንስ መግቢያ ገንዘብ ክፍያ ለመክፈል የተፈቀደው ተጨማሪ ጊዜ 30 ቀን ነው ። በኢንሹራንስ መግቢያ ገንዘብ ብድር ፤ ወይም ውሉ እንዲቀር በሚያደርገው የውሉ ቃል መሠረት ጸንቶ እንዲቀጥል ካልሆነ በቀር የኢንሹራንስ መግቢያ ገንዘብ ወይም በየጊዜው የሚከፈለው የኢንሹራንስ መግቢያ ገንዘብ መከፈል በነበረበት ቀን ወይም በተጨማሪው ጊዜ ውስጥ ያልተከፈለ እንደሆነ ፤ መጥሪያ መስጠት ወይም ሌላ ዓይነት ሥነ ሥርዓት መከተል ሳያስፈልግ ይህ ፖሊሲ ዋጋ ያጣል » ይህ የፖሊሲ ድንጋጌ ትንታኔ የሚፈልጉ ሁለት አግባብ ያላቸው ነጥቦች ይዟል ። ይኸውም ፤

ሀ. የኢንሹራንስ ውል ማደሻ ገንዘብ ለመክፈል ባለኢንሹራንሱ 30 ቀን ተጨማሪ ጊዜ ይሰጣል ።

ለ. የኢንሹራንስ ውል ማደሻው ገንዘብ መክፈያ ቀን ሲደርስ ባለኢንሹራንሱ ክፍያ አይጠይቅም ፤ ነገር ግን ሕጉ የኢንሹራንስ ውል ማደሻ ገንዘብ ክፍያ መጠየቅን የባለኢንሹራንሱ ግዴታ አድርጎታል ።

ሕጉ ፤ የኢንሹራንስ ውል ማደሻ ገንዘብ ያለመክፈልን ውጤት ፖሊሲው ጸንቶ የቆየበትን ጊዜ ግምት ውስጥ በማስገባት ይከፋፍለዋል ። ይኸውም ለሶስት ዓመት ጊዜ አከፋፈል የተመደቡ ገንዘቦች ያነሰ የተከፈለበትና ቢያንስ ለሶስት ዓመት አከፋፈል የተመደቡ ገንዘቦች የተከፈሉበት በማለት ነው ። ይሁንና በነዚህ ሁለት ጊዜያት ሕጉ በባለኢንሹራንሱ ላይ ክፍያ የመጠየቅን ግዴታ ይጭንበታል ። ቁጥር 709/2/ እንዲህ ይላል ፤ «ስለሆነም በየዓመቱ ለሶስት ዓመት ጊዜ አከፋፈል የተመደቡ ገንዘቦች ያነሰ የተከፈለ ሆኖ በየዓመቱ የሚከፈለው ገንዘብ በተወሰነው ጊዜ ያልተከፈለ እንደሆነ ፤ ኢንሹራንስ ሰጪው እንዲከፈለው መጠየቅና ጠይቆም ለማግኘት ያልቻለ እንደሆነ ፤ ጥያቄ ካደረገ ከአንድ ወር በኋላ ውሉን ማፍረስ ይችላል ።» ቁጥር 709/3/ ደግሞ ፤ « በየዓመቱ ለሶስት ዓመት ጊዜ አከፋፈል የተመደቡ የኢንሹራንስ ገንዘቦች ከተከፈሉና በየዓመቱ የሚከፈለው ገንዘብ በተወሰነው ጊዜ ውስጥ ያልተከፈለ እንደሆነ ፤ ኢንሹራንስ ሰጪው እንዲከፈለው ከጠየቀበት ጊዜ አንስቶ በአንድ ወር ያልተከፈለ እንደሆነ የኢንሹራንሱ ውል ውድቅ አይሆንም ። ባለኢንሹራንሱ ማድረግ የሚችለው ለተከፈለው ገን

ዘብ[21] የኢንሹራንስ ውል ፖሊሲ መስጠት ወይም በውል የተስማሙበትን ዋና ገንዘብ ወይም በየጊዜው በሕይወት እስካለ ድረስ የሚከፈለውን ገንዘብ በቁጥር 656 በተመለከተው መሠረት መቀነስ ብቻ ነው ።» ይላል ። በመሆኑም ፤ ኢንሹራንስ ሰጪው ክፍያ የመጠየቅ ግዴታ እንዳለበት ሕጉ ሲደነግግ ፖሊሲው ደግሞ የኢንሹራንስ ውል ማደሻ ገንዘብ መክፈያ ዕለት ሲደርስ ፣ ኢንሹራንስ ሰጪው ክፍያ አይጠይቅም ይላል ። ይህ ኢንሹራንስ ሰጪው ወይም ሕግ አዋቂው በአፋጣኝ መፍትሔ ሊሹለት የሚገባ ጉዳይ ነው ።

## የፕሪሚየም ክፍያ መቋረጥ በሕይወት ኢንሹራንስ ፖሊሲ ላይ የሚያስከትለው ውጤት ፤

### የሕይወት ኢንሹራንስ ጠቅላላ ድንጋጌ

ለኢንሹራንስ ውል ማደሻ ገንዘብና በየጊዜው ለሚከፈለው የኢንሹራንስ መግቢያ ገንዘብ መክፈያ 30 ቀን ተጨማሪ ጊዜ ይፈቀዳል።

የኢንሹራንስ ገንዘብ በተጨማሪ ጊዜ ውስጥ ያልተከፈለ እንደሆነ ኢንሹራንስ ሰጪው ክፍያ አይጠይቅም ፤ ፖሊሲው ያለምንም ማስታወቂያ ውድቅ ይሆናል ።

### የንግድ ሕግ ድንጋጌ

1. ለሶስት ዓመት ጊዜ አከፋፈል ከተመደበው ገንዘብ ያነሰ የተከፈለ እንደሆነ ፤
   ሀ/ ኢንሹራንስ ሰጪው ክፍያ ይጠይቃል ።
   ለ/ ጥያቄ ከቀረበበት ከአንድ ወር በኋላ ውሉን ማፍረስ ይችላል ።
2. ለሶስት ዓመት ጊዜ አከፋፈል ከተመደበው ገንዘብ የበለጠ የተከፈለ እንደሆነ ፤
   ሀ/ ኢንሹራንስ ሰጪው ክፍያ ይጠይቃል ።
   ለ/ ጥያቄ ከቀረበ ከአንድ ወር በኋላ ክፍያ ያልተደረገ እንደሆነ ፤ ኢንሹራንስ ሰጪው(1) ለተከፈለው ገንዘብ የኢንሹራንስ ውል ፖሊሲ ይሰጣል ወይም (2) በየጊዜው በሕይወት እስካለ ድረስ የሚከፈለውን ገንዘብ በቁ. 656 (1) መሠረት ይቀንሳል ።

ስለአታላይነት[22] የሚናገረው የሕይወት ኢንሹራንስ ፖሊሲ ጠቅላላ ድንጋጌ እንዲህ ይላል ፤« የኢንሹራንስ ውል ፖሊሲ ከጸናበት ቀን ጀምሮ በሁለት ዓመት ውስጥ ውል ለመዋዋል ሀሳብ ባቀረበው ሰው ወይም በኢንሹራንስ ገቢው ሆነ ተብሎ የተደረገ አታላይነት መኖሩ የተረጋገጠ እንደሆነ ፤ በዚህ ፖሊሲ ውስጥ ከተገለጸው ከማናቸውም ግዴታ ድርጅቱ ነፃ ነው ። በመሆኑም ኢንሹራንስ ገቢው የከ

ፈለውን ወይም ከኢንሹራንስ ሰጪው ይከፈለው የነበረውን ማናቸውንም ገንዘብ ያጣል ።» ይሁን እንጂ ፖሊሲው በመቀጠል እንዲህ ይላል «፤የኢንሹራንሱ ውል ፖሊሲ ከጸና ከሁለት ዓመት በኋላ ኢንሹራንስ ገቢው ባልተገለጸው ነገር ምክንያት የሞተ እንደሆነ ድርጅቱ ውሉ በተመሠረተበት እለት የሚከፈለውን የኢንሹራንስ ዋጋ ወይም የተከፈለውን ጠቅላላ የኢንሹራንስ መግቢያ ገንዘብ ፤ ከሁለቱ ብዛት ያለውን ፤ ማናቸውንም ተጨማሪ የኢንሹራንስ መግቢያ ገንዘብ ሳይጨምር በመክፈል ብቻ ይወሰናል ።«ኢንሹራንስ ገቢው በሕይወት ባለበት በማናቸውም ጊዜ የተደበቀው ነገር የተገለጸ እንደሆነ ድርጅቱ ባለው የኢንሹራንስ ውል ደንብ መሠረት የኢንሹራንስ መግቢያውን ገንዘብ ያስተካክለዋል ።

የዚህን ድንጋጌ የመጨረሻ ክፍል በሚመለከት ረገድ ልዩነቱን ማስተዋል ይቻላል ። ሕጉ ፤ መሸሸጉ አደጋ[23] ከመድረሱ በፊት የተገለጸ እንደሆነ ኢንሹራንስ ሰጪው ከአንድ ወር ማስታወቂያ በኋላ ውሉን ማፍረስ ወይም የኢንሹራንስ መግቢያ ገንዘብ ተጨምሮ ውሉ እንዲቀጥል ለማድረግ ይችላል ሲል ይደነግጋል ። ነገር ግን ፖሊሲው የተደበቀው ነገር ፤ ኢንሹራንስ ገቢው በሕይወት እያለ የተገለጸ እንደሆነ የኢንሹራንስ ሰጪውን ከአንድ ወር ማስታወቂያ በኋላ የማፍረስ መብት ወደ ጐን የተወው ይመስላል ።ለኢንሹራንስ ሰጪው የተሰጠው መብት ባለው የኢንሹራንስ ውል ደንብ መሠረት የኢንሹራንስ መግቢያውን ገንዘብ ማስተካከል ብቻ ነው ።

## 6. ተደራራቢ ኢንሹራንስ

ሕጉና ፖሊሲው የማይጣጣሙበትና ትክክለኛውን ሁኔታ የማያንጸባርቁበት ሌላም ክፍል አለ ። ይኸውም ስለ ተደራራቢ ኢንሹራንስ የሚናገረው ክፍል ነው ። የአካል አደጋ ኢንሹራንስ ፖሊሲ ክፍል 3 እንደሚከተለው ይደነግጋል ፤ « ... ... ... ኢንሹራንስ ገቢው ይህን የኢንሹራንስ ፖሊሲ ከተቀበለ ወይም እንዲጸና ካደረገ በኋላ በማንኛውም ጊዜ ድርጅቱ በጽሑፍ ሳይስማማ ከሌላ ኢንሹራንስ ሰጪ ጋር በአካል አደጋ ችሎታ ማጣት ወይም የሞት ኢንሹራንስ ውል የተዋዋለ እንደሆነ ይህ ፖሊሲ ፍጹም ዋጋ ያጣል ፤ ይህን በሚመለከት ረገድ ምንም ዓይነት የመብት ጥያቄ አይኖርም[24]። » አያሌ ኢንሹራንስ ሰጪዎች አንዱን ዕቃ ለአንዱ ዓይነት ጉዳት ኢንሹራንስ በመስጠታቸው ኢንሹራንስ የገባው ዕቃ ዋጋ ኢንሹራንስ ከተደረገበት ዋጋ የበለጠ ሲሆን እያንዳንዱ የኢንሹራንስ ሰጪ በኢንሹራንስ ገቢው በኩል ማታለል ከተደረገ ውሉ እንዲፈርስና ኪሣራም እንዲከፈለው መጠየቅ ይቻላል ። ኢንሹራንስ የገባው ሰው በቅን ልቡና ያደረገው እንደሆነ በአደጋ ጊዜእያንዳንዱ ኢንሹራንስ ሰጪ ስለኢንሹራንሱ በተዋዋለበት ሂሳብ መጠን ካሣ ከፋይ ይሆናል[25]። ፖሊሲው በአጠቃላይ ያለድርጅቱ የጽሑፍ ስምምነት ከሌላ ኢንሹራንስ ሰጪ ጋር ስለመዋዋልና ስለውጤቱ ሲናገር ሕጉ ግን በማታለል የተደረገና በቅን ልቡና የተደረገ በማለት ከሁለት ይከፍለዋል ። በሚከተለው ማጠቃለያ መግለጫ በቀላሉ ቀርቧል።

ተደራራቢ ኢንሹራንስ በሕጉና በኢንሹራንስ ፖሊሲው የሚያስከትለው ውጤት

| | በፖሊሲው ያለው ውጤት |
| --- | --- |
| ኢንሹራንስ ገቢው አንድ ፖሊሲ ከጸና በኋላ ያለድርጅቱ የጽሑፍ ፈቃድ አንድ ዕቃ ለአንዱ ዓይነት ጉዳት ፤ ከሌላ ኢንሹራንስ ሰጪ ጋር የተዋዋለ እንደ ሆነ ፤ | ፖሊሲው ፍጹም ዋጋ ያጣል ፤ ይህን በሚመለከት ረገድ ምንም ዓይነት የመብት ጥያቄ አይኖርም። |

| | በሕጉ ያለው ውጤት |
|---|---|
| ስለ አንዱ ዕቃ ለአንዱ ዓይነት ጉዳት ከአያሌ ኢንሹራንስ ሰጪዎች በማታለል መዋዋል ። | እያንዳንዱ ኢንሹራንስ ሰጪ ውሉ እንዲፈርስና ኪሣራም እንዲከፈለው ይጠይቃል ። |
| ተደራራቢው ኢንሹራንስ የተደረገው በቅን ልቦና ሲሆን ፤ | እያንዳንዱ ኢንሹራንስ ሰጪ አደጋ በደረሰ ጊዜ ስለኢንሹራንሱ በተዋዋለ በት ሂሳብ መጠን ካሣ ይከፍላል ። |

ከዚህ በላይ ከሰፈረው መግለጫ ማየት እንደምንችለው በሕጉና በፖሊሲው መካከል አለመጣጣም ከመኖሩም በላይ በሕጉም ሆነ በፖሊሲው ስለተደራራቢ ኢንሹራንስ የተነገረው ጊዜው ያለፈበት ነው ። ሁለቱም ከአዋጅ ቁጥር 26/1967 መንፈስና ዓላማ ጋር አብረው አይሄዱም ። ኢኮኖሚውን ማኅበራዊ ለማድረግ በተደረገው ሙከራ ፤ መሠረታዊ የሆኑት የምርት መገልገያዎች ሁሉ እንደ መሬት ፤ ፋብሪ ካዎች ፤ ማዕድናት ወዘተ ያሉት የሕዝብ ንብረት ሆነዋል ። በአዋጅ ቁጥር 26/1967 ክፍል 2(ፐ) መሠረት ሙሉ በሙሉ የመንግሥት ከሆኑት ድርጅቶች አንዱ ኢንሹራንስ ነበር ። ይህ ወደ አንድ ዓቢይ ማጠቃለያ ይመራናል ፤ ይኸውም ሁሉም የኢንሹራንስ ድርጅቶች በመንግሥት ቁጥጥር ሥር ከመሆናቸውም በላይ ሁሉም ቅርንጫፎች በብሔራዊ ኢንሹራንስ ድርጅት ሥር ተደራጅተዋል። በመሆኑም አንድን ዕቃ ለአንድ ዓይነት ጉዳት ኢንሹራንስ ያስገባ ማንኛውም ሰው ይህንኑ ዕቃ ለተመሳሳይ ጉዳት ከሌላ ኢንሹራንስ ሰጪ ዘንድ ኢንሹራንስ ሊያስገባው አይችልም ፤ ምክንያቱም በአሁኑ ጊዜ ኢትዮጵያ ውስጥ አንድ ኢን ሹራንስ ሰጪ ብቻ ነው ያለው ። ይኸውም ብሔራዊ የመድን ድርጅት ነው ። ለሥራ ቅልጥፍናና የደንበኞችን መጨናነቅ ለማስወገድ ሲባል ይህ ድርጅት አያሌ ቅርንጫፎች ፤ ለምሳሌ አፍሶል ቅርንጫፍ ፤ አንበሳ ቅርንጫፍ ፤ ናይል ቅርንጫፍ ፤ የመሳሰሉትን በውስጡ ይዟል ።

## ማ ጠ ቃ ለ ያ

ኢትዮጵያ የሶሻሊስት የዕድገት መንገድ ለመከተል ስለአወጀች ለድሮው ሁኔታ ተስማሚ የነበሩ ተቋሞችና ሕጎች ጊዜው ያለፈባቸው ይመስላሉ ። ምንም እንኳ በሁለቱ መካከል በይነ—ግብር መኖሩ የማይዘነጋ ቢሆንም ላዕላይ—መዋ ቅሩ ታሕታይ—መዋቅሩን ማንጸባረቅ አለበት ። የቀድሞዎቹ ሕጎችና ተቋሞች ከአዲሱ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ሁኔታ ጋር መስማማት አለባቸው ስንል የቀድሞዎቹ ሕጎችና ተቋሞች በሙሉ ይቅሩ ማለታችን አይደለም ። አጠናክረን ለመናገር የምንሞክረው ከአዲሱ ማኅበራዊ ሁኔታ ጋር የሚስማሙትንና አግባብ ያላቸውን ነገሮች ማቆየት ፤ ከአዲሱ ሥርዓተ ማኅበር ዓላማና መንፈስ ጋር አብረው የማይ ሄዱትንና የድሮውን ማኅበራዊ ግንኙነት ዕድሜ ለማራዘም አስተዋጽኦ የሚያ ደርጉትን ነገሮች መተው እንዳለብን ነው ። እርግጥ ፤ በፖሊሲውና በሕጉ ውስጥ ያሉትን አግባብነት የሌላቸውን ነገሮች መተው ቀላል አይደለም ። በብዙ አቅ ጣጫ ጥናትና ምርምር ማድረግን የሚጠይቅ ነው ።

የዚህ ጽሑፍ ዋና ዓላማ በንግድ ሕግ የኢንሹራንስ ድንጋጌዎችና በኢንሹ ሹራንስ ፖሊሲ መካከል ያለውን አለመጣጣም መጠቆም ነው ። እንዲህ ያለው ችግር እንዴት መቃለል አለበት? ሕጉን መለወጥ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ፤ የኢን ሹራንስ ንግድን እንደሚስማማና የኢንሹራንስ ገቢውን ሕጋዊ ጥቅሞች እንደ ሚጠብቅ ሆኖ መለወጥ አለበት ። በእርግጥ ሕጉ መለወጥ አለበት ፤ ለምን ቢባል ፤ በአንድ በኩል የሕግ ድንጋጌዎች በሌላ በኩል ደግሞ መሠረታዊ የሆኑትን የሕ ጉን ድንጋጌዎች የሚሽሩ የውል ቃሎችና የውል ሁኔታዎች በአንድነት መኖር የለባቸውም ።

መቸም በአንድ በኩል የሁለቱን ወገኖች ግንኙነትና ሕጋዊ ግዴታ የሚመ ለከቱ የፖሊሲ ድንጋጌዎች እርስ በርስ ሳይጣጣሙ ሁለቱም ጐን ለጐን አብረው መቆየት እንደማይችሉ ግልጽ ነው ። ለዚህ መፍትሔ ሊሆን የሚችለው ፤

ሀ. ፖሊሲዎቹም ሆኑ ሕጉ የንግድን ተጨባጭ ሁኔታ እንዲያንጸባርቁ አድርጐ ማስተካከል ነው ። ይህም ሲሆን በሕጉና በፖሊሲው ውስጥ ያሉትን ድን ጋጌዎች እንዲጣጣሙ ማድረግን ይጠይቃል ።

ለ. የተለያዩ የፖሊሲ ድንጋጌዎችን በመለወጥ ከሕጉ ጋር እንዲስማሙ ማድ ረግ ፤ ይህ ካልሆነ ግን ለወደፊት አብረው መሄድ የማይችሉና አቅጣጫቸው የተለያየ የፖሊሲና የሕግ ድንጋጌዎች ሳይስማሙ እንዳሉ እንዲቆዩ ያደ ርጋል ።

# የግርጌ ማስታወሻዎች

* በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፣ ሕግ ፋኩልቲ ሌክቸረር (ለጥናት በማጊል ዩኒቨርሲቲ ይገኛሉ ።)

1. ፕሬስተንና ኮሊንሾ ፣ ሎውስ ኦፍ ኢንሹራንስ ፣ ገጽ 1
2. ብርሃኑ ኪዳኔ ፣ ኢንሹራንስ ዳሜጅስ ኢን ኢትዮጵያ ፣ ኮምፐንሴሽን ኦር ሚትስ ፡ ገጽ 11.
3. አዋጅ ቁ. 26 ማርች 11/1975
4. ፒተር ዊንሺፕ ፣ ባክግራውንድ ዶኩመንትስ ኦፍ ዘ ኢትዮጵያን ኮመርሻል ኮድ ፤ እ. አ. አ. 1960 ገጽ 80
5. የፍ/መዝገብ ቁ. 1099(1965/እ. ኤ. አ)
6. የፍት/ይግባኝ መዝገብ ቁ. 1184/1965(እ. ኤ. አ)
7. የእሳትና የመብረቅ ውል አንቀጽ (11)
9. ፒተር ዊንሺፕ ፣ ባክግራውንድ ዶኩመንትስ ኦፍ ዘ ኢትዮጵያን ኮመርሻል ኮድ 1960 ገጽ 86
10. ለሁሉም ዓይነት አደጋ ፖሊሲ ፣ የማይወሰድ ሁኔታ ቁ.9 ፣ ኮንስኮንሻል ኪሣራ ፖሊሲ ሁኔታ ቁ. 11 ፣ 15 ፣ የሠራተኛ ካሣ ፖሊሲ ሁኔታ ቁ. 10 ፣ የቤት ሥርሠራና ቤት ሰብሮ የመግባት ፖሊሲ ቁ. 8

11ሀ. የፍት/መዝ/ ቁ. 1166/ 1974 (እ.ኤ.አ.)

11. የንግድ ሕግ ቁ. 668 ን ይመለከቷል ።
12. ዲስዳሌ እና ማክሙርዶ ፣ ኤለመንትስ ኦፍ ኢንሹራንስ ገጽ 84
13. የኢትዮጵያ ንግድ ሕግ ቁ. 668(2)
14. ከዚያው ቁ. 668(2) (ለ)
15. ኮንስኮንሻል ሎስ ፖሊሲ ኮንዲሽን ቁ. 1 ፤ መኒ ፖሊሲ ኮንዲሽን ቁ. 3. 6 ፤ ፓብሊክ ላያቢሊቲ ፖሊሲ ኮንዲሽን ቁ. 12 ፣ በርግለሪ ፖሊሲ ኮንዲሽን ቁ. 2.
16. ማክጊልብረይ ፣ ኢንሹራንስ ሎው ፣ ቮልዩም 1 — ቁ. 893
17. የኢትዮጵያ የንግድ ሕግ ቁጥር 668 እና 669 ይመለከቷል ።
18. አሰገደች እንዳይላሉ ፣ ከሳሽ ፣ የኢምፔሪያል ኢንሹራንስ ኩባንያ መልስ ሰጭ ፤ የፍትሐብሔር መዝገብ ቁጥር 1055/59
19. ወ/ሮ ቅድስት ከሳሽ ሚቸል ኮትስ ተከሳሽ የፍትሐብሔር መዝገብ ቁ. 1001/61
20. የኢትዮጵያ የንግድ ሕግ ፤ 1960 ቁ. 669 (3)
21. ሉተከፈለው ገንዘብ የኢንሹራንስ ውል መስጠት ፣ የኢንሹራንሱ ውል እንደጸና ቢቀጥል ኖሮ ውሉ በሚፈጸምበት ዕለት ወይም ኢንሹራንስ ገቢው ከተጠቃሚው አስቀድሞ የሞተ እንደሆን የሚከፈል ከነበረው ያነሰ የገንዘብ መጠን ነው ። ለተከፈለው ገንዘብ የኢንሹራንስ ውል የሚሰጠው ፣ ቢያንስ ለሶስት ዓመት ጊዜ አከፋፈል የተመደቡ ገንዘቦች ተከፍለው ፣ ኢንሹራንስ ገቢው በተለያዩ ምክንያቶች የኢንሹራንስ መግቢያ ገንዘብ ለመክፈል ያልፈለገ ወይም ያልቻለ እንደሆነ ነው ። ስለዚህም ፣ ኢንሹራንስ ገቢው ውል በሚፈጸምበት ዕለት ወይም ከተጠቃሚዎቹ አስቀድሞ የሞተ እንደሆነ ይከፈለዋል ።

    የተከፈለው ገንዘብ ዋጋ የተከፈለበት ዓመት ብዛት ፖሊሲው ጸንቶ የቆየበት ጊዜ መድን የተሰጠበት ገንዘብ መጠን የተከፈለ ገንዘብ ዋጋ ፖሊሲው በተሰረዘበት ዕለት ከሚከፈል ጥሬ ገንዘብ የተለየ ነው ። ውሉ በተሰረዘበት ዕለት የሚከፈል የኢንሹራንስ ዋጋ ማለት የኢንሹራንሱ ውል እንደጸና ቢቀጥል ኖሮ ይከፈል ከነበረው ያነሰ ፖሊሲው በሚሰረዝበት ጊዜ የሚከፈል የገንዘብ መጠን ነው ። በአጠቃላይ ግን አነስተኛ መጠን ያለው የተከፈለ ገንዘብ ዋጋ እየተባለ ይጠራል ፤ ምክንያቱም የክፍያው ጊዜ እስከ ውሉ መፈጸሚያ ዕለት ስለሚቆይ ነው ። ኢንሹራንስ ገቢው የኢንሹራንስ መግቢያ ገንዘብ መክፈል ካቋረጠበትና ስለዚሁ ማስታወቂያ ከደረሰው እስከ ሶስት ወር ድረስ ለተከፈለው ገንዘብ የኢንሹራንሱ ውል በተሰረዘበት ዕለት ጥሬ ገንዘብ የመጠየቅ መብት አለው (የሕይወት ኢንሹራንስ ፖሊሲ ቁጥር 4 ፣ ጠቅላላ ድንጋጌ ይመለከቷል ።)

22. የሕይወት ኢንሹራንስ ፖሊሲ ጠቅላላ ድንጋጌ ቁ. 10
23. የኢትዮጵያ ንግድ ሕግ ቁጥር 668 ፤
24. የግል መኪና አጠቃላይ ፖሊሲ ፣ ሁኔታ ቁ. 6 ፤ የሁሉም ዓይነት አደጋ ፖሊሲ ሁኔታ ቁ. 7 ፣ ኮንስኮንሻል ኪሣራ ፖሊሲ ሁኔታ ቁ. 2 ፣ 12 ፣ የሠራተኛ ካሣ ፖሊሲ ሁኔታ ቁ. 11 ፤ የንግድ ተሽከርካሪ ፖሊሲ ፤ ሁኔታ ቁ. 6 ፣ የቤት ሥርሠራና ቤት ሰብሮ የመግባት ፖሊሲ ፤ ሁኔታ ቁ. 8 ፤
25. የኢትዮጵያ ንግድ ሕግ ቁ. 681